ሞዓ አንበሳ

'Moa Anbessa'

ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል

The Conquering Lion

Ethiopians For Constitutional Monarchy

መግለጫ

=====

መስከረም 16 ቀን 1985 ዓም በዋሽንግተን ዲሲ ካፒታል ሒልተን የስብሰባ አዳራሽ በተካሄደው ዓመታዊ ስብሰባ የወጣ መግለጫ።

1. ዘውድ የኢትዮጵያ ታሪካዊ መታወቂያ በመሆኑ የሺህ ዘመናት ሥርወ መንግሥቱን ተክትሎ ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ የሕዝቧን ልዕልና የአገሪቱን ሉዓላዊነት ሲጠብቅና ሲያስከብር የኖረ በመሆኑ አሁንም ወደ ጥንተ ክብሩ እንዲመለስ እንጠይቃለን።

2. ግርማዊ ቀዳማዊ አምኃ ሥላሴ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰልፍ በጠየቀው መሠረት የሽግግሩ መንግሥት እንዲተባበርና የግርማዊነታቸው መመለስ እንዲፋጠን እንቅፋትና መሰናክሎችን ሁሉ በማስወገድ የሕዝቡን ፍላጎት እንዲያሟላ ምቹ ሁናቴንም እንዲፈጥር አጥብቀን እንጠይቃለን።

3. የግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ አጽም በህይወታቸው ሳሉ ባሠሩት መካነ መቃብር በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን በተገቢ ማዕረግና ክብር እንዲቀበር ከዚህ ቀደም በሞዓ አንበሳ ተደጋግሞ የቀረበውን ጥያቄ በሙሉ ልብ እንደግፋለን። እኚህ ታላቅ የኢትዮጵያ፣ የአፍሪካና የዓለም መሪ የሚገባቸውን ክብርና ግርማ ሞገስ የሽግግሩ መንግሥት ሊነፍጋቸው መቃጣቱን እናወግዛለን።

4. አሁን በመረቀቅ ላይ ያለው ሕገ መንግሥት ድርሰት ብቻ እንዳይሆን፤ የኮሚሽኑ አባላት ሁሉን አቀፍ ማለት ያገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የኪነ ጥበብ ሰዎች፣ የደራሲያን፣ የጀግኖች፣ የጋዜጠኞች፣ የሠራተኞች ወዘተ...ባለሙያዎችን ሁሉ ያካተተ እንዲሆን እንጠይቃለን።

P.O. Box 38, Oakton, Virginia 22124 • Tel. No. (703) 264-0197

5. ባሁኑ ሰዓት ያለው የሽግግር መንግሥት መሥራች ድርጅቶች ጥለውት የወጡ ስለሆነና በቅርቡም የተደረገው የክልል ተወካዮች ምርጫ ያልተስተካከለና የዲሞክራሲ ይዘትየጎደለው በመሆኑ በሁለ ዘንድ በተለይ በውጭ ተመልካቾች በመወገዙ ሁሉን የሚያካትት ብሔራዊ ጉባኤ እንዲደረግ ከያለበት የሚሰማውን ጥያቄ እንደግፋለን።

6. በኤርትራ ውስጥ በተናጠል ሕዝበ ወሳኔ (Referendum) ለማካሄድና ኤርትራን እንደገና ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ርምጃ በመወሰድ ላይ መሆኑ ታውቋል። ይሁንና ይህ ርምጃ ሕዝቡን በማይወክሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ብቻ የሚካሄድ ነው። ስለሆነም ከዚህ ውሳኔ ከመደረሱ በፊት በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚወክለው ሕጋዊ መንግሥት መኖርና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሁናቴው መክሮና ዘክሮበት ያልተደረገ ውሳኔ ሊፀና አይችልም ሕጋዊነትም አይኖረውም። ስለዚህ ይህን አፈጻጸም አበክረን እናወግዛለን።

7. በዘርና በሃይማኖት በማከፋፈል የሚካሄደውን ጦርነት ግድያና ዝርፊያ በጥብቅ እናወግዛለን።

8. ፓርቲ በርዕዮተ ዓለምና በፕሮግራም የሚደራጅ እንጅ በዘር፣ በጎሣና በሃይማኖት መሆን የለበትም። ይህንኑም የሚያራምዱ ድርጅቶችንና ቡድኖችን እናወግዛለን።

9. በሐረር፣ በአርሲና በሲዳሞ እንዲሁም በሌሎችም ክፍለ ሀገሮችና ጠቅላይ ግዛቶች ውስጥ በአማራው ኅብረተሰብ ላይ የደረሰው ኢሰብአዊ ግፍና፣ ቂም በቀል የተመላበት ጭፍጨፋ እጅግ የሚዘገንን ነው። ይህንኑ ድርጊት በፈፀሙትና ባስፈፀሙት ላይ አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድ እንጠይቃለን። የተፈፀመውንም አሰቃቂ ግድያ እናወግዛለን።

10. በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች ከተሞች እንደዚሁም በየጠቅላይ ግዛት ባሉ አባላትና የጽ/ቤት ተጠሪዎች ላይ የሚደረግባቸው ተጽእኖ መታሠር፣ መንገላታትና ዛቻ ሁሉ በአስቸኳይ እንዲቆም እናሳስባለን።

11. የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁንም ሰው ሰራሽ በሆነው የእርስ በርስ ግጭትና የተፈጥሮም ችግር ተጨምሮበት በረሀብ በእርዛትና ሰላም ማጣት ምክንያት ከኑሮው እየተፈናቀለ በስደትና በልዩ ልዩ ስቃይ ላይ ስለሆነ የዓለም በጎ አድራጎት ድርጅቶች በተለይም የአሜሪካንና የምዕራባውያን መንግሥታት እርዳታቸውን ከመለገስ እንዳያቋርጡ አደራ እንላለን።